**City of Cambridge**

# DHSP የልጅ እንክብካቤ እና የቤተሰብ ድጋፍ
# የቅድመ-ትምህርት ቤት ዕጣ
# ተደጋግመው የሚነሱ ጥያቄዎች

## የDHSP ቅድመ-ትምህርት ቤት ዕጣ ውስጥ ለመግባት ብቁ ማነው?

የዕድሜ መስፈርቱን የሚያሟሉ ልጆች ያሏቸው የካምብሪጅ ነዋሪዎች የ DHSP ቅድመ-ትምህርት ዕጣ ውስጥ መግባት ይችላሉ። ለ2023-2024 የትምህርት ዓመት ምዝገባ የኦክቶበር 2022 ዕጣ፣ የልደት ቀናቸው ከኤፕሪል 1/2019 እስከ ዲሴምበር 5/2020 ድረስ የሆኑ ህጻናት ዕድሜያቸው ብቁ እንደሆነ ይቆጠራል።

## የDHSP ቅድመ-ትምህርት ቤቶች ዕጣ ውስጥ እንዴት እገባለሁ?

መስከረም 2023 ለሚጀምረው የትምህርት ዓመት የዕጣ ማመልከቻዎች የሚገቡት ኦክቶበር 2022 ወር ውስጥ ነው። ለቅድመ-ትምህርት ቤት ምዝገባ ልጅዎ ብቁ ሆኖ የሚገኘው እድሜው 2 ዓመት ከ 9 ወር - 4 ዓመት ከ 5 ወር ከሆነ ነው። **ለምሳሌ ኦክቶበር 2022 ላይ የሚኖረው ዕጣ ውስጥ ለመግባት (ለ 2023-2024 የትምህርት ዓመት ምዝገባ)፣ የልጅዎ የልደት ቀን ከኤፕሪል 1/2019 እስከ ዲሴምበር 5/2020 ድረስ መሆን ይኖርበታል።**

የዕጣ ማመልከቻዎ እንደተሟላ እንዲታሰብ የሚከተሉትን ሰነዶች ማስገባት ይኖርብዎታል።

- **የDHSP ቅድመ-ትምህርት ዕጣ ማመልከቻ**
- **የገቢ መጠን እና የቤተሰብ ብዛት ማረጋገጫ፡-** የግብር ተመላሽ **እና** 4 ተከታታይ የደምወዝ ወረቀቶች (ወይም ያለፉት 30 ቀናት) **ወይም** እየተቀበሉዋቸው ላሉ ማንኛውም ዓይነት ጥቅማ ጥቅሞች ወቅታዊ የሽልማት ደብዳቤዎች (TANF፣ SSI፣ SNAP፣ WIC፣ ወዘተ.)
- **የልጅ ዕድሜ ማረጋገጫ፡-** የልጅ የልደት የምስክር ወረቀት **ወይም** የልጅ ፓስፖርት
- **የአድራሻ ማረጋገጫ፡-** የኪራይ ውል፣ የቤት ማስያዣ፣ ከቤቶች አቅራቢ የተላከ ደብዳቤ፣ ባለፉት 2 ወራት ውስጥ የታተመ የፍጆታ ክፍያ፣ ባለፉት 2 ወራት ውስጥ የታተመ የኬብል ክፍያ፣ አሽከርካሪ የተመዘገበበት ወረቀት፣ **ወይም** የጥገኝነት ቅጽ

## ለDHSP ቅድመ-ትምህርት ቤት ዕጣ የት ማመልከት እችላለሁ?

የ DHSP የቅድመ ትምህርት ዕጣ ማመልከቻ በኦክቶበር ወር ውስጥ በwww.cambridgema.gov/presschoollottery ላይ ይገኛል።

በአካል ተገኝቶ እርዳታ የሚሰጥ ሰው በጥያቄዎ መሠረት ይገኛል። አስፈላጊ ከሆነ፣ እባክዎ dhsppreschools@cambridgema.gov ወይም 617-349-6254 ተጠቅመው ያነጋግሩ።

## የ DHSP ቅድመ-ትምህርት ቤት ዕጣ የሚካሄደው እንዴት ነው?

በእያንዳንዱ የቅድመ-ትምህርት መማሪያ ክፍሎቻችን ውስጥ ግማሽ የሚሆኑ በታዎችን ቅድሚያ ለሚሰጣቸው ቤተሰቦች እንይዛለን። ቅድሚያ የሚሰጣቸው ቤተሰቦች ብለን የምንገልፃቸው ከ U.S. የቤቶች እና የከተማ ልማት አከባቢ አማካኝ ገቢ (HUD AMI) 65% ወይም በታች የሆኑ ቤተሰቦችን ነው። (**የ2022 HUD AMI የገቢ ቻርትን ይመልከቱ**) የዕጣ ማመልከቻዎች እንደደረሱን እና የማመልከቻ ሂደቱ ከተዘጋ በኋላ ማመልከቻዎች የተሟሉ መሆናቸውን እና የቅድሚያ ተሰጪነት ሁኔታን እንገመግማለን እንዲሁም እንደ አስፈላጊነቱ ቤተሰቦችን እንከታተላለን። በተጨማሪም በዚህ ጊዜ በእያንዳንዱ የመማሪያ ክፍል ውስጥ ለዕጣ ምደባ ክፍት የሆኑ ስንት አጠቃላይ እና ቅድሚያ ለሚሰጣቸው የተዘጋጁ ቦታዎች እንደሚኖሩን እንወስናለን።

የዕጣው ተሳታፊዎች ስብስብ ከተሟላ እና ለተከታዩ የትምህርት ዓመት የሚኖሩንን ክፍት በታዎች ብዛት ካወቅን በኋላ ዕጣ ማውጣቱ ይካሄዳል።

በመጀመሪያ መስፈርቱን ለሚያሟሉ ቅድሚያ ለሚሰጣቸው ቤተሰቦች የተዘጋጁትን ቦታዎች ለመስጠት በዘፈቀደ ቁጃኑዋሪ ማመንጫ ዕጣ ይወጣል። ለእያንዳንዱ ቤተሰብ ዕጣ ሲወጣ የመጀመሪያ ምርጫቸውን ተመልክተን እዛ የመማሪያ ክፍል ውስጥ ክፍት ቦታ ካለ እንመድባቸዋለን። የመጀመሪያ ምርጫቸው ውስጥ ክፍት ቦታ ከሌለ፣ ሁለተኛ ምርጫቸውን እንመለከታለን። እንዲህ እያልን በዚህ መልኩ እንቀጥላለን። የመረጧቸው መርሃ-ግብሮች አንዳቸውም ክፍት ቦታ ከሌላቸው ቅድምያ የሚሰጣቸው ጠባቂዎች ስብስብ ውስጥ እንዲካተቱ ይደረጋል።

ቅድሚያ ለሚሰጣቸው አመልካቾች ከሚደረገው ዕጣ በኋላ፣ በአሁኑ ጊዜ የ DHSP ቅድመ-ትምህርት መማሪያ ክፍል ውስጥ የተመዘገበ እህት ወይም ወንድም ያላቸው አመልካቾች ላይ ትኩረት እናደርጋለን። እህትማማቾች እና ወንድማማቾች የመረጡት የመማሪያ ክፍል ውስጥ ክፍት ቦታ ካለ እዛ ይመደባሉ።

በመቀጠል፣ የዘፈቀደ ቁጃኑዋሪ ማመንጫ በመጠቀም እስካሁን ቦታ ላልተሰጣቸው ቤተሰቦች የአጠቃላይ ቦታዎች ዕጣ እናወጣለን። ለእያንዳንዱ ቤተሰብ ዕጣ ሲወጣ የመጀመሪያ ምርጫቸውን ተመልክተን እዛ የመማሪያ ክፍል ውስጥ ክፍት ቦታ ካለ እንመድባቸዋለን። የመጀመሪያ ምርጫቸው ውስጥ ክፍት ቦታ ከሌለ፣ ሁለተኛ ምርጫቸውን እንመለከታለን። እንዲህ እያልን በዚህ መልኩ እንቀጥላለን። የመረጧቸው መርሃ-ግብሮች አንዳቸውም ክፍት ቦታ ከሌላቸው ቅድምያ የሚሰጣቸው ጠባቂዎች ስብስብ ውስጥ እንዲካተቱ ይደረጋል።

ከዕጣ ማውጣቱ ሂደት በኋላ፣ የቅድመ-ትምህርት ርዕሰ-መምህራን ጋር የሚገኙትን የክፍል ዝርዝሮች በመመልከት ወደ ከመጠን ያለፈ ምዝገባ የሚወስዱ ስህተቶች አለመፈጠራቸውን እናረጋግጣለን። ዝርዝሮቹን ካረጋገጥን በኋላ ቤተሰቦች ለቅደመ-ትምህርት ቤት ዕጣ በሚያመለክቱበት Viewpoint በሚባለው የኦንላይን መድረክ ላይ የዕጣውን ውጤት ለቤተሰቦች እናሳውቃለን። ቦታ የተሰጣቸው ቤተሰቦች የቅድመ-ትምህርት ቤቱን መገኛ፣ ቦታውን መሠረት ያደረጉ ጥያቄዎችን ለመጠየቅ እና/ወይም የጉብኝት ዕቅድ ለማስያዝ እንዲችሉ የመገኛ አድራሻውን እና የክፍያውን መጠን እንዲያውቁ ይደረጋል።

ውድቅ የተደረጉ ቦታዎች መኖራቸውን ስንረዳ ቅድሚያ ከሚሰጣቸው ጠባቂዎች ስብስብ ውስጥ እያወጣን ያሉበት ሁኔታ ለውጥ ካለው ቤተሰቦችን በ Viewpoint እናሳውቃለን።

## በ DHSP ቅድመ-ትምህርት ውስጥ ቦታ የማግኘት እድሌን እንዴት መጨመር እችላለሁ?

ብዙ መርሃ-ግብሮችን በመረጡ ልክ ቦታ የማግኘት ዕድልዎ የተሻለ ይሆናል። በሰዓቶች ወይም በመገኛ በታቸው ምክንያት ልጅዎን ሊልኩባቸው የማይችሏቸው ማንኛውም መርሃ-ግብሮች ካሉ እባክዎ **አይምረጧቸው**። ለመረጡት ማንኛውም መርሃ-ግብር ከተመረጡ እና ያንን ቦታ ውድቅ ካደረጉ በዕጣ ውስጥ ያሎትን ቦታ ያጣሉ። ወደ ሌላ መርሃ-ግብር ዝውውር መጠየቅ አይችሉም።

## ልጄ በDHSP ቅድመ-ትምህርት ቤት ውስጥ ቦታ ማግኘቱን የማውቀው መቼ ነው?

ዕጣውን ተከትሎ በዲሴምበር ወር ያውቃሉ።

## በ DHSP ቅድመ-ትምህርት ቤት ውስጥ ቦታ ከተሰጠኝ ልጄን ማስመዝገብ እንደምፈልግ ማሳወቅ አለብኝ?

አዎ። ሁሉም ቦታ የተሰጣቸው ቤተሰቦች እስከ ጃኑዋሪ 31/2023 ድረስ ቦታውን እንዲቀበሉ ወይም ውድቅ እንዲያደርጉ ይጠየቃሉ። እስከ ጃኑዋሪ 31[ቀን] ድረስ ከቤተሰብ ምላሽ ካላገኘን ቦታውን ጠባቂ ዝርዝር ውስጥ ላለ ሌላ ተማሪ እንሰጣለን።

## የ DHSP ቅድመ-ትምህርት ዕጣ ውስጥ እህቶች እና ወንድሞች ያሏቸው በተለየ ይመረጣሉ?

በአንዱ የቅድመ-ትምህርት መርሃ-ግብራችን ውስጥ አሁን ላይ ተመዝገበው የሚገኙ እህትና ወንድም ያሏቸው ተማሪዎች ዕጣው በሚወጣበት ጊዜ ቅድሚያ ይሰጣቸዋል ነገር ግን በእርግጠኝነት ቦታ ያገኛሉ ማለት አይደለም።

## የ ካምብሪጅ ነዋሪ ካልሆንኩ ነገር ግን የ City of Cambridge ወይም የ Cambridge Public Schools ተቀጣሪ ከሆንኩ ልጄን የDHSP ቅድመ-ትምህርት ቤት ዕጣ ውስጥ ማስገባት እችላለሁ?

እንደ ሁልጊዜው፣ የካምብሪጅ ነዋሪዎች ቅድሚያ የምንሰጣቸው ናቸው። የካምብሪጅ ነዋሪ ያልሆኑ የ City of Cambridge እና የ Cambridge Public Schools ተቀጣሪዎች ለ2023 – 2024 የትምህርት ዓመት ምዝገባ፣ ኦክቶበር 2022 ላይ የሚኖረው ዕጣ ውስጥ መግባት ይችላሉ።

የካምብሪጅ ነዋሪ ያልሆኑ የ City of Cambridge ወይም የ Cambridge Public Schools ተቀጣሪዎች ዕጣ ውስጥ መግባት ስለመቻላቸው በየዓመቱ ከዕጣው በፊት እንገመግማለን። የካምብሪጅ ነዋሪ ያልሆኑ የ City of Cambridge ወይም የ Cambridge Public Schools ተቀጣሪዎች በአድራሻ ማረጋገጫ ሰነዶች ምትክ የተቀጣሪነት ማረጋገጫ ማስገባት ይጠበቅባቸዋል።

## ለDHSP ዕጣ የጠባቂ ስብስብ ውስጥ ከተካተትኩ ምን ማድረግ አለብኝ?

በታዎች ሲገኙ ክፍት በታውን ለማቅረብ ጠባቂ ስብስብ ውስጥ ያሉ ቤተሰቦችን እንገናኛለን። ለሚቀጥለው ዕጣ (ኦክቶበር 2023) ማመልከቻዎችን መቀበል እስክንጀምር ድረስ የጠባቂ ስብስቡ ባለበት ይቆያል። ጠባቂ ስብስቡ ኦክቶበር 2023 ላይ ጊዜው ያበቃና ዕድሜያቸው አሁንም ብቁ የሆኑ ልጆች ያሏቸው ቤተሰቦች ለቀጣዩ ዓመት ምዝገባ ወደ ዕጣው በድጋሚ እንዲገቡ እንቀበላቸዋለን።

አማራጭ መርሃ-ግብሮችን ለማግኘት እርዳታ ካስፈለግዎ ቅድመ-ትምህርት ቤቶችን ለማግኘት የሚከተሉት ግብዓቶች አሉ።

- Find It Cambridge: finditcambridge.org or 617-686-2998
- Birth to 3rd Partnership: cpsd.us/departments/b3 ወይም 617-349-6554
- Department of Early Education and Care (የቅድመ ትምህርት እና እንክብካቤ መምሪያ): eeclead.force.com/EEC_ChildCareSearch
- የቤተሰቦች ማዕከል፦ 617-349-6385

## በ DHSP ቅድመ ትምህርት ቤት ለመግባት ምን ያህል ያስከፍላል?

የ DHSP ቅድመ -ትምህርት ቤት የክፍያ መጠኖች የገቢ መጠንን መሠረት በሚያደርግ ተንሸራታች የዋጋ ሚዛን ይወሰናሉ። የዋጋ ሚዛኑ በ የዓመቱ ከ DHSP ቅድመ-ትምህርት ዕጣ ቁሳቁሶች ጋር አብሮ ይለቀቃል።

በሰብአዊ አገልግሎት መርሃ-ግብሮች መምሪያ ውስጥ መርሃ-ግብሮቻችን ለሁሉም የካምብሪጅ ቤተሰቦች ተደራሽ እንዲሆኑ ለማድረግ እንተጋለን። ቫውቸርስ እንቀበላለን እንዲሁም ብቁ ሆነው ለሚገኙ ቤተሰቦች የጎላ የትምህርት ክፍያ ድጋፍ እናቀርባለን። የሚደረገው የትምህርት ክፍያ ድጋፍ መጠን ጠቅላላ የቤተሰብ ገቢ፣ የቤተሰብ ብዛት እና የግል ችግርን መሠረት ያደረገ ነው።

ለ2023 – 2024 የትምህርት ዓመት የትምህርት ክፍያ የዋጋ መጠናችን፦

| ጠቅላላ የቤተሰብ ገቢ | የተጠጋጋ<br>ዕለታዊ የትምህርት ክፍያ መጠን** | ወርሐዊ የትምህርት ክፍያ መጠን |
|---|---|---|
| $252,401 – በላይ | $84.94 | $1,840.42 |
| $189,301 - $252,400 | $67.95 | $1,472.33 |
| $151,441 - $189,300* | $50.97 | $1,104.25 |
| $126,201 – $151,440* | $40.77 | $883.40 |
| $0 - $126,200* | የግዛቱ መነሻ ዕለታዊ የትምህርት ክፍያ መጠን $63.22 ነው። ከ$0 እስከ $189,300 ጠቅላላ የገቢ መጠን ያላቸው ሁሉም ቤተሰቦች ከግዛቱ ዕለታዊ የክፍያ መጠን | |

| | |
|---|---|
| | በታች እንዲከፍሉ በ City of Cambridge ድጎማ ይደረግላቸዋል። ከ $0 እስከ $126,200 ጠቅላላ የገቢ መጠን ያላቸው ቤተሰቦች ለተጨማሪ የትምህርት ክፍያ ድጋፍ ብቁ ይሆናሉ። የሚደረገው የትምህርት ክፍያ ድጋፍ መጠን ጠቅላላ የቤተሰብ ገቢ፣ የቤተሰብ ብዛት እና የግል ችግርን መሠረት ያደረገ ነው። ስለ የግል ስኮላርሺፕ የዋጋ መጠኖች ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ ያነጋግሩን። |

**የትምህርት ክፍያ የሚከፈለው በወርሃዊ የክፍያ መጠን መሠረት ነው። ዕለታዊ የክፍያ መጠን በወር ውስጥ በአማካይ 22 የሚከፈልባቸው ቀናት መኖራቸውን መሠረት በማድረግ ይሰላል።

## ለስኮላርሺፕ እንዴት ማመልከት እችላለሁ?

ምንም ተጨማሪ ወረቀት መሙላት አያስፈልግዎትም! ዕጣው ውስጥ ለመግባት የሚያስገቡዋቸውን ሰነዶች የክፍያ መጠን እንዲሁም የትምህርት ክፍያ ድጋፍ ለማስላት እንጠቀማቸዋለን።

## ከፍተኛውን ክፍያ የምከፍል ከሆነ የገቢ መጠን እና የቤተሰብ ብዛት ማረጋገጫ ማስገባት ይኖርብኛል?

የገቢ መጠንዎ ከፍተኛ የሚባለው የመጠን ክልል ውስጥ ከሆነ፣ የገቢ መጠንም ሆነ የቤተሰብ ብዛት ማረጋገጫ ማስገባት አይጠበቅብዎትም። የልጅዎን ዕድሜ እና አድራሻ ግን ማረጋገጥ ያስፈልግዎታል።

## የ DHSP ቅድመ-ትምህርት ቤቶች የስራ ሰዓታት ስንት ናቸው?

ሁሉም የ DHSP ቅድመ-ትምህርት ቤቶች በዓመት 12 ወራት እና በሳምንት 5 ቀናት (ሰኞ - አርብ) ይሰራሉ። Haggerty, Kennedy/Longfellow, M.L. King እና Windsor ቅድመ-ትምህርት ቤቶች ከ7:30 a.m. – 5:30 p.m. ድረስ ይሰራሉ።

King Open፣ Morse፣ እና Peabody ቅድመ-ትምህርት ቤቶች ከ8:00 a.m. – 6:00 p.m. ድረስ ይሰራሉ።

## በ DHSP ቅድመ-ትምህርት ቤቶች ውስጥ ማንኛውም የትርፍ ሰዓት ቦታዎች ይኖራሉ?

በየትኛውም መርሃ-ግብሮቻችን ውስጥ የትርፍ ሰዓት ቦታዎችን አንሰጥም። ሁሉም ቦታዎች በሳምንት ለ5 ቀናት እና በዓመት ለ12 ወራት የሚሆኑ ናቸው።

## በአሁኑ ጊዜ የ DHSP ቅድመ-ትምህርት ቤቶች ምን የ COVID-19 ጥንቃቄዎች ይወስዳሉ?

የ COVID-19 ስርጭትን በመከላከል ዙሪያ ሳይንሱ እየተቀየረ ሲመጣ የምንተገብራቸው ልዩ ጥንቃቄዎች እና ሂደቶች ይለወጣሉ። ቅድሚያ የምንሰጠው ለልጆቻችን፣ ለቤተሰቦቻችን እና ለሠራተኞቻችን ጤና እና

ደህንነት ነው። ስለዚህም የ COVID-19 መመሪያዎችን ለመተግበር እና ለመከተል እንዲሁም ለመርሃ-ግብሮቻችን ውሳኔዎችን ለመወሰን ከካምብሪጅ የህዝብ ጤና መምሪያ ጋር በቅርበት እንሰራለን። በዚህ ጊዜ, በፕሮግራሞቻችን ውስጥ ጭምብሎች አማራጭ ናቸው። ከካምብሪጅ የህዝብ ጤና፣ ከካምብሪጅ የህዝብ ትምህርት ቤቶች እና/ወይም ከቅድመ-ትምህርት እና እንክብካቤ ክፍል (EEC) መመሪያ ሲቀየር እኛም እንዲሁ መመሪያችንን እንቀይራለን።